# እ.ኤ.አ ከጁን 1-10/2018 የነበረው


# የአየር ሁኔታ ግምገማ

ባለፈው ጁን የመጀመሪያው አሥር ቀናት ለክረምት ዝናብ መስፋፋትና መጠናከር አመቺ ሁኔታን የሚፈጥሩ የሚቲዎሮሎጂ ክስተቶች ከቀን ወደ ቀን በምዕራብ አጋማሽና በመካከለኛው የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ የተሻለ ገጽታ እንደነበራቸው መረጃዎች ያሳያሉ። ከዚሁም ጋር ተያይዞ በአንዳንድ ቦታዎች ላይ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ ተመዝግቧል። ከባድ መጠን ያለው ዝናብ ከመዘገቡ ጣቢያዎች መካከል ለመጥቀስ ያህል በአቦቦ 33.7፣ በአይራ ፣31.2 በአምቦ 68.2፣ በአርጆ 36.4 ፣46.4፣ 54.2 እና 36.4 በአሶሳ 47.4፣ በአዴት 30.3፣ በአየሁ 31.8፣ በቤጊ 39.7፣ በብላቴ 33.2፣ 47.4፣ በቦሬ 77.6፣ 43.8፣ በቻግኒ 51.1 በጪራ 49.0 ፣ በጋምቤላ 36.7፣ በጊምቢ 76.0፣ 40.9፣ በጊኒር 45.0 በጎሬ 34.4 ፣በሀገረማርያም 32.5፣ በክብረመንግስት 34.0፣ 61.1፣ በቁሉምሳ 31.3፣ በሊሙገነት 38.6፣ በላይበር 54.2፣ በሞጣ 42.0፣ 50.6 በመካነሰላም 51.7፣ 59.6፣ በነጆ 67.1፣ 35.9 በነቀምቴ 38.4 በሾላ ገበያ 33.1፣ 31.1 በሰኮሩ 36.4፣ በወላይታ ሶዶ 72.1፣ 41.4 ፣34.6 እና 43.0 በዝዋይ 36.4 በወራቤ 34.2፣ እና በማጂ 32.3 በፉኚዶ 51.1 እና በእምድብር 61.4፣ 30.2፣ 36.1 በሚ.ሜትር ይገኙበታል።


ባለፉት አሥር ቀናት የዘነበው የዝናብ መጠን ከሀገሪቱ የቦታ ሽፋን አንጻር ሲገመገም በምዕራብና መካከለኛው አማራ፤ በደቡብ ቤንሻንጉል ጉሙዝ፤ በምዕራብ፣ በሰሜንና በመካከለኛው ኦሮሚያ፤ በአዲስ አበባ፤ ከደቡባዊው ብሔር ብሔረሰቦችና ህዝቦች ደቡባዊው ክፍል በሰተቀር ሁሉም የክልሉ ዞኖች ከ50-221 ሚ.ሜትር የደረሰ ዝናብ ከ6-10 ቀናት ያህል ዝናብ እንዳገኙ መረዳት ተችሏል (ካርታ 1 እና 2) ።

ባለፉት አሥር ቀናት የዘነበው የዝናብ መጠን ከመደበኛው ጋር ሲነጻጸር የመካከለኛው፣ የምሥራቅና የደቡብ ትግራይ ዞኖች፤ ከአማራ ክልል የደቡብ ጎንደር እንዲሁም ከጥቂት የሰሜን ጎንደር ዞን በስተቀር፣ የባህር ዳር ዙሪያ፣ የምሥራቅና የምዕራብ ጎጃም፣ አዊ ዞን፣ የሰሜንና የደቡብ ወሎ አብዛኛው ዞኖች እንዲሁም የሰሜን ሸዋ ዞን፤ ከቦረና ደቡባዊ ክፍልና ከጥቂት የባሌ ኪስ ቦታዎች በስተቀር ሁሉም የኦሮሚያ ዞኖች፤ አዲስ አበባ፤ በደቡባዊው ብሔር ብሔረሰቦችና ህዝቦች ከቤንች ማጂ ምዕራባዊ ክፍል በስተቀር፤ ጋምቤላና አብዛኛው የአፋር ዞኖች መደበኛና ከመደበኛ በላይ ዝናብ ነበራቸው (ካርታ 3)፡፡


ካርታ 1   እ.ኤ.አ ከጁን 1 እስከ 10 /2018 ድረስ የነበረው የዝናብ መጠን በሚ.ሜ



ካርታ 2   እ.ኤ.አ ከጁን 1 እስከ 10 /2018 ድረስ የነበረው የዝናብ መጠን በሚ.ሜ



ካርታ 3   እ.ኤ.አ ከጁን 1 እስከ 10 /2018 ድረስ የነበረው የዝናብ መጠን
ከመደበኛው ጋር በመቶኛ ሲነፃፀር





ከመደበኛ በታች    መደበኛ    ከመደበኛ በላይ

# <u>እ.ኤ.አ ከጁን 1-10/2018 የነበረው የአየር ሁኔታ</u>

# <u>በእርሻው ሥራ እንቅስቃሴ ላይ ያሳደረው ተጽዕኖ</u>

ባለፉት የጁን የመጀመሪያው አሥር ቀናት በክረምት ዝናብ ተጠቃሚ በሆኑ ቦታዎች ላይ በስርጭትም ሆነ በመጠን ጥሩ የሆነ እርጥበት ሁኔታ ነበራቸው፡፡ ይህም አብዛኛው የክረምት ዝናብ ተጠቃሚ አካባቢዎችን ያዳረሰዉ እርጥበት ለመኸር የእርሻ ስራ እንቅስቃሴ፣ ለማሳ ዝግጅት፣ ለቋሚ ተክሎች፣ ለረጅም ጊዜ ሰብሎች የዉሃ ፍላጎት መሟላትና ለአርብቶ አደሮችና ከፊል አርብቶ አደር አካባቢዎች ለመጠጥ ውሃ ፍላጎት መሟላት፣ ለግጦሽ ሳር ልምላሜ፣ እድገታቸውን ላልጨረሱና ፍሬ በማፍራት ላይ ለነበሩ የበልግ ሰብሎች አዎንታዊ ጠቀሜታ ነበረው፡፡ በተጨማሪም በአንዳንድ ቦታዎች ላይ አልፎ አልፎ የነበረው ከባድ መጠን ያለው ዝናብ ለአብዛኛው የእርሻ እንቅስቃሴ ጠቀሜታው የጎላ የነበረ ቢሆንም፤ በተወሰኑ ቦታዎች ላይ አሉታዊ ጎን ነበረዉ ከነዚህም ዉስጥ በመካነ ሰላም ጁን 4 እና 5 በተከታታይ የጣለው ከፍተኛ ዝናብ ጎርፍ በማስከተል በንብረት ላይ ጉዳት አድርሷል (ካርታ 4)፡፡

ካርታ 4 እ.ኤ.አ ከጁን 1 እስከ 10/2018 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ





# <u>እ.ኤ.አ ከጁን 01-10/2018 የነበረው የአየር ሁኔታ</u>

## በውሃው ዘርፍ እንቅስቃሴ ላይ ያሳደርው ተፅዕኖ

እ.ኤ.አ ከጁን 01 እስከ 10 ጁን 2018 የነበረው የአየር ሁኔታ በውሃው ዘርፍ እንቅስቃሴ ላይ የነበረውን ሁኔት ስንመለከት የተሻለ የእርጥበት መጠን በአብዛኛው አባይ፣ ኦሞጊቤ፣ ስምጥሸለቆ፣ የደቡባዊ አጋማሽ ገናሌዳዋ፣ የላይኛው ባሮአኮቦ እና መካከለኛው ዋቢሸበሌ የደቡባዊ ተፋሰሶች ከፍተኛ እርጥበት አግኝተዋል$ በተጨማሪም እርጥበታማና መጠነኛ እርጥበት የተሰተዋለባቸው ተፋሰሶች ምዕራባዊ የአገሪቱ ተፋሰሶችና በጥቂት መካከለኛው ክፍል የሚገኙ ሲሆኑ እነዚህም ምዕራባዊ አጋማሽ ተከዜ፣ የታችኛው ባሮአኮቦ፣ የላይኛው ኦሞጊቤ፣ ምእራብ አባይ አዋሳኝ ከፍተኛ ቦታዎች፣ የታችኛው ኦሞጊቤ እና በጥቂት የታችኛው ስምጥሸለቆ ተፋሰሶች ናቸው$ በተቀሩት በአብዛኛው የሀገሪቱ ተፋሰሶች ላይ በከፊል ደረቅና ደረቅ ሁኔታ አመዝኖ ተሰተውሏል$ በተለይ በሰሜን ምስራቅ፣ በምስራቅ እንዲሁም በመካከለኛው የሀገሪቱ ተፋሰሶች ላይ የነበረው ደረቅ ሁኔታ ከቀኑ ሙቀት ጋር ተዳምሮ በውሃ ሀብት ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ ነበረው (ካርታ 5) $

ካርታ 5 እ.ኤ.አ ከጁን 1 እስከ 10/2018 ድረስ በተፋሰሶች ላይየነበረው የእርጥበት መጠን



# <u>እ.ኤ.አ ከጁን 11-20/2018 የሚኖረው</u>

# <u>የአየር ሁኔታ አዝማሚያ</u>

በጁን ሁለተኛው አሥር ቀናት በመደበኛ ሁኔታ በደቡብ ምዕራብ፣ በምዕራብ፣ በሰሜን ምዕራብና በመካከለኛው አካባቢዎች ላይ ዝናብ ሰጭ የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች እየተጠናከሩ የሚሄዱ ሲሆን፤ በአንጻሩ በሰሜንና በሰሜን ምሥራቅ ላይ አልፎ አልፎ ከሚኖረው መጠነኛ ዝናብ በስተቀር ደረቅና ሞቃታማ የአየር ሁኔታ ያመዝናል።

በሚቀጥሉት አሥር ቀናት ለክረምት ዝናብ መፈጠር አስተዋጽኦ የሚያደርጉ የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች ከቀን ወደ ቀን እየተጠናከሩ እንደሚሄዱ ስለሚጠበቅ፤ በብዙ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ የተሻለ የዝናብ መጠንና ሥርጭት ሊኖር እንደሚችል የትንበያ መረጃዎች ይጠቁማሉ።

በአጠቃላይ በሚቀጥሉት አሥር ቀናት <u>ከኦሮሚያ ክልል ምሥራቅ እና ምእራብ ወለጋ፣ ጅማ፣ ኢሉአባቦራ፣ አብዛኛዎቹ የሸዋ ዞኖች፣ ምዕራብ እና ምሥራቅ ሐረርጌ እንዲሁም የአርሲና ባሌ ዞኖች ፤ አዲስ አበባ፤ ከአማራ ክልል ምዕራብና ምሥራቅ ጎጃም፣ የሰሜንና የጎንደር ዞኖች፣ የባህር ዳር ዙሪያ፣ ሰሜን ሸዋ እንዲሁም የሰሜንና የደቡብ ወሎ ዞኖች፤ ሁሉም የትግራይ ዞኖች፤ ከአፋር ዞን 3 እና 5 ፤ የጋምቤላና የቤንሻንጉል ዞኖች በተጨማሪም ከደቡብ ብሄር ብሄረሰቦችና ህዝቦች ክልል የሀዲያና የጉራጌ፣ የወላይታ፣ የከፋና የቤንች ማጂ፣ ሲዳማ እንዲሁም ጥቂት የሰገን ህዝቦች ዞኖች ከመደበኛው ጋር የተቀራረበና አልፎ አልፎም በጥቂት ቦታዎቻቸው ላይ ከመደበኛ በላይ ዝናብ ያገኛሉ። በተጨማሪም ከሚጠናከሩ የደመና ክምችቶች በአንዳንድ ሥፍራዎች ላይ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ ሊከሰት ይችላል። በአንጻሩ የተቀሩት የሀገሪቱ ዞኖች ግን ደረቅ ሆነው ይሰነብታሉ።</u>

# <u>እ.ኤ.አ. ከጁን 11-20/2017 የሚኖረው የአየር ሁኔታ አዝማሚያ</u>

# <u>በእርሻው ሥራ እንቅስቃሴ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተጽዕኖ</u>

ከላይ በተሰጠው የአስር ቀን ትንበያ መሠረት ለዝናብ መፈጠር አስተዋጽኦ የሚያደርጉ የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች ከቀን ወደ ቀን እየተጠናከሩ እንደሚሄዱ መረጃዎች ይጠቁማሉ፡፡ ይህም ሁኔታ በክረምት ተጠቃሚ አካባቢዎች ላይ ለሚጠበቀው የግብርና

እንቅስቃሴ ጥሩ ጎን እንደሚኖረዉ ይጠበቃል፡፡ በአጠቃላይ ከላይ በትንበያው ላይ በተጠቀሱት አካባቢዎች በአብዛኛው ከመደበኛው ጋር የተቀራረበ ዝናብ የሚያገኙ ሲሆን፣ ከዚህም ጋር ተያይዞ የሚጠበቀው ዝናብ የአፈር ውስጥ እርጥበትን ከማሻሻል አንፃር አስቀድመው የተዘሩና በተለያየ የዕድገት ደረጃ ላይ ለሚገኙ የበልግም ሆነ የረጅም ጊዜ የመኸር ሰብሎች እንዲሁም ለተለያዩ የቋሚ ተክሎችና የጓሮ አትክልቶች የውሀ ፍላጎታቸውን ከማሟላት አንፃር ከፍተኛ ጠቀሜታ ይኖረዋል፡፡ በአንፃሩ በአንዳንድ አካባቢዎች ላይ የሚጠበቀው ከባድ ዝናብ በተለይም ባሳለፍናቸው ቀናት በተከታታይ ዝናብ በማግኘት ላይ በሚገኙ ቦታዎች ላይ የአፈር ውስጥ እርጥበት መብዛት፣ እንዲሁም ለጎርፍ ተጋላጭ በሆኑ አካባቢዎች ከአፈር መሸርሸርም ሆነ ከመሬት መንሸራተት ጋር የተያያዙ ችግሮችን ሊያስከትል ስለሚችል አስፈላጊውን ጥንቃቄ ማድረግ ተገቢ ነዉ፡፡ በተጨማሪም የሚጠበቀው ዝናብ የደረሱ የበልግ ሰብሎች ላይ ጉዳት እንዳያደርስ ተገቢዉን ጥንቃቄ በማድርግ በመካከል በሚገኙ ደረቅ ቀናት የሰብል ስብሰባ ተግባራትን ማከናወን ያስፈልጋል፡፡ በሌላ በኩል በአርብቶ አደርና ከፊል አርብቶ አደር አካባቢዎች የሚጠበቀው እርጥበት በመጠን ዝቅተኛ ቢሆንም፤ በተለይም ባሳለፍናቸው ቀናት አካባቢዎቹ ካገኙት የተሻለ እርጥበት ጋር ተዳምሮ የመጠጥ ውሀ አቅርቦትንም ሆነ የግጦሽ ሳር ልምላሜና የተፈጥሮም ሆነ የሰው ሰራሽ ምንጮችን ከማጎልበት አንጻር ጥሩ ጎን ይኖረዋል፡፡ ከዚህም ጋር ተያይዞ ለአርብቶ አደርና ከፊል አርብቶ አደር አካባቢዎች ጥሩ አስተዋጽኦ እንደሚኖረዉ ይጠበቃል፡፡

## እ. ኤ. አ ከጁን 11-20/2018 የሚኖረው የአየር ሁኔታ

## አዝማሚያ በውሃው ዘርፍ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ

በሚቀጥሉት አስር ቀናት ውስጥ የክረምቱ እርጥበታማ ሁኔታ ባብዛኛው የሀገሪቱ ተፋሰሶች ላይ እየተሰፋፋ በመሄድ የክረምት ዝናብ ተጠቃሚ የሆኑት ተፋሰሶች ላይ የተሻለ እርጥበት ሊኖር እንደሚችል የትንበያ መረጃዎች ያመለክታሉ$

በመሆኑም በአብዛኛው ኦሞጊቤ" ባሮአኮቦ፣ ተከዜ" የላይኛው አዋሽ" ዋቢሸበሌ" የገናሌዳዋ እና የላይኛውና መካከለኛው ስምጥሸለቆ ተፋሰሶች ከመደበኛ ጋር የተቀራረበ ዝናብ የሚያገኙ ሲሆን፤ አልፎ አልፎ በጥቂት ቦታዎች ላይ ከመደበኛ በላይ የሆነ ዝናብ ሊኖራቸው ይችላል። በተጨማሪም የአዋሽና የምስራቃዊው አባይ አዋሳኝ ተፋሰሶችና በጥቂት የመካከለኛው አዋሽ፣

የላይኛው ተከዜና አፋር ደናከል አዋሳኝ ከፍተኛ ቦታዎች በጥቂት ቦታዎቻቸው ላይ አነስተኛ መጠን ያለው ዝናብ እንደሚኖራቸው ይጠበቃል$ ከዚህ ጋር ተያይዞ የመሬት ሽፋኑ የሳሳ በመሆኑ አልፎ አልፎ የሚከሰተው ከባድ ዝናብ ቅፅበታዊ ጎርፍ ሊያስከትል ስለሚችል ቅድመ ጥንቃቄ ማድረግ አሰፈላጊ ነው። የተቀሩት የሀገሪቱ ተፋሰሶች ላይ ከፊል ደረቅና ደረቅ የአየር ሁኔታ አመዝኖባቸው ይቆያል።